# የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ወጪና ገቢ ዕቃዎች በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ስለመጠቀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 134/2013 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 135/2013

በወጪና ገቢ እቃዎች ማጓጓዝ ሂደት የሚፈፀሙትን ወንጀሎች ለመቆጣጠር እንዲያስችል የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ለመጠቀም አስገዳጅ መመሪያ መውጣቱን ተከትሎ በመመሪያው የተቀመጠው የካፒታል መጠን ለአቅራቢነት የሚያመለክቱ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች የአቅም ውስንነት በመታየቱ፤
የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት እና በዘርፉ ፍትሐዊ የንግድ ውድድር እንዲኖር በማስቻል ለአቅራቢነት የሚያመለክቱ ፍላጐቱ ያላቸውን ሁሉ ያማከለ እና አሳታፊ እንዲሆን መመሪያውን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 20(2) በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 112 (2) እና አንቀጽ 107 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ወጪና ገቢ ዕቃዎች በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ስለመጠቀም የወጣውን መመሪያ ቁጥር 134/2013 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 135/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

1) በመመሪያው አንቀጽ 2 የትርጉም ክፍል ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ ቁጥር 28 ተጨምሯል

28.“ካፒታል” ማለት ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ለአቅራቢነት የሚያመለክተው ሰው ከንግድ ስራው ጋር በተያያዘ የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ፣ ሕንጻ፣ የስራ ማስኬጃ እና አጠቃለይ የንግድ ሀብቱን ያጠቃልላል፡፡

2) **የመመሪያው አንቀጽ** 12 ንዑስ አንቀጽ (1) “ለ” እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

ለ. ከብር 5,000,000.00 (አምስት ሚሊዮን) ያላነሰ ካፒታል ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ፣

3) **የመመሪያው አንቀጽ** 12 ንዑስ ቁጥር 2 ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡፡

2. አቅራቢው ወይም ሰራተኞቹ አገልግሎት ሰጪዎቹና ተቋሙ ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው በህግ ለሚጣልባቸው መቀጫ የሚውል የ2 ሚሊዮን ብር የባንክ ወይም የመድን ዋስትና የሚያቀርብ፣

4) **በመመሪያው አንቀጽ** 16 (1) ስር የሚከተሉት አዲስ ተራ ፊደሎች ሠ እና ረ ተጨምረዋል፡፡

ሠ. ስለሚያቀርባቸው መሣሪያዎችና ስለሚያገኛቸው አገልግሎቶች ከአምራቹ ጋር ቢያንስ ለ5 ዓመት የገባውን የስምምነት ሰነድ እና

ረ. ስለመሣሪያው አለም አቀፍ ብቃት ማረጋገጫ በአባሪ I እና II መሠረት በቦርድ የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟላ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

3.. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

መመሪያው በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክቶሬት ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ …………….. ቀን 2004 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክቶሬት

## አባሪ 3

## Annex III

Supplier Requirements listed down under annx III No 3.1 & 3.2 are repealed and replaced by the following

| | Criteria | unit | Description |
|---|---|---|---|
| 3.1 | Four wheel pickup Trucks | Qty. minimum 2 | Service vehicles |
| 3.2 | Installation/Service Center | Qty 1 | A plot of land owned or rented for this purpose or a garage which will be deployed to the same purpose rented from other garage owners. |